# የአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት ብቻ የሚውሉ ልዩ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ለመፍቀድ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 230/2013

የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች በተሽከርካሪ በማገዝ ከቦታ ወደቦታ በመንቀሳቀስ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ወስጥ ተገቢውን ተሳትፎ በማድረግ ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ ማግኘት ተገቢውን እገዛ ማድረግ እንዳለበት በማመኑ፣

አካል ጉዳተኞች ወደአገር የሚያስገቧቸው ልዩ ተሽከርካሪዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተሰጠው መብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ሚያረጋግጥ የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ______________ አንቀጽ ___________ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት ብቻ የሚውሉ ልዩ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲያስገቡ ለመፍቀድ የወጣ መመሪያ ቁጥር 230/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ወስጥ

1. “አካል ጉዳተኛ” ማለት በተፈጥሮው፣ በሕመም ወይም በማናቸውም አደጋ ምክንያት ለዘለቄታው የአካል ጉዳት የደረሰበት፣ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገው፣ እና የደረሰበትን የአካል ጉዳት በዝርዝር የሚያሳይ በሐኪሞች ቦርድ የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ሰው ነው፡፡

2. “ልዩ ተሽከርካሪ” ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሊያሽከረክረው የሚችለው ለአካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሆኖ ባለሁለት እግር፣ ባለሦስት እግር ወይም ባለአራት እግር ማኪናን የሚጨምር ሲሆን፣ የእነዚህ ተሽከርካሪዎች የሞተር ጉልበት በማናቸውም ሁኔታ ከ1600 ሲሲ (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሲሲ) መብለጥ የለበትም፡፡

3. "የመቡቱ ተጠቃሚ" ማለት የአካል ጉዳተኛ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ ተሽከርካሪን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት የሚጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት የሚችል ግለሰብ ነው፡፡

4. "የግል አገልግሎት" ማለት የመብት ተጠቃሚው ልዩ ተሽከርካሪውን በራሱ አሽከርካሪነት ለግል ጉዳዮች ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ ማጠቀም ሲሆን በማቸውም ሁኔታ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ፣ ለንግድ ሥራ ዓላማ ወይም ገቢ ለሚገኝበት ማንኛውም ተግባር ማዋልን አይጨምርም፡፡

5. "የሐኪሞች ቦርድ" ማለት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እውቅና በተሰጠው ሆስፒታል የተቋቋመ እና የአካል ጉዳተኝነት ሚያረጋግጫ ሠርተፊኬት ወይም ማስረጃ ማስጠት የሚችል አካል ነው፡፡

6. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለሥልጣኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

7. "ሚኒስቴር እና ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒቴርና ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

8. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጉምሩክ አዋጅ፣ በጉምሩክ ቀረጥና ማስከፈያ ደንብ ወይም ሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ቅደመ ሁኔታዎች ለሚያሟሉ አካል ጉዳተኞች ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን በምቹ ሁኔታ በማንቀሳቀስ ማከናወን እንዲችሉ ለማገዝ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## <u>ልዩ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ለማስገባት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

## 5. <u>ልዩ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማስገባት</u>

የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ አሟልቶ ሲቀርብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከቱት ልዩ ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንድ ልዩ ተሽከርካሪ ብቻ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

## 6. ልዩ ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ማንኛውም የመብቱ ተጠቃሚ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ማሟላት አለበት፡፡

1. በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን እና በሀገር ውስጥ ከሚኖርበት አካባቢ የሚመለከተው አስተዳደር የተሰጠ የነዋሪነት መታወቂያ ማቅረብ፣

2. በአገር ውስጥ ከሚገኝ እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እውቅና ከተሰጠው ሆስፒታል አካል ጉዳተኛ መሆኑን እና የጉዳቱን ዓይነት የሚያረጋግጥ በሐኪሞች ቦርድ የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ፣

3. ከሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኝነት ማረጋገጫ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ፣

4. በስሙ የሚያስመጣውን ተሽከርካሪ እራሱ አካል ጉዳተኛው ሊጠቀምበት እንደሚችል ከሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ወይም መ/ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ እና የታደሰ የመንጃ ፍቃድ ማቅረብ፣

5. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካርድ (TIN) ማቅረብ፣

6. ተሽከርካሪውን ለመግዛት የሚችል መሆኑን ከሚከተሉት አማራጮች በአንዱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

   ሀ) የመብት ተጠቃሚ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም በጡረታ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት የተከፈለው ደመወዝ ወይም የጡረታ አበል ለባለሁለት እና ለባለሦስት እግር ልዩ ተሽከርካሪ ሲሆን የተጣራ ገቢው ቢያንስ 40,000 ብር (ብር አርባ ሺህ) እና ባለአራት እግር ተሽከርካሪ ሲሆን ደግሞ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 80,000 ብር (ብር ሰማንያ ሺህ) መሆን ያለበት ሲሆን ከቀጣሪው አካል ወይም ከሚመለከተው የጡረታ አስተዳደሪ አካል የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Payroll) ወይም ከጡረታ አስተዳዳሪው አካል ከተሰጠ ማረጋገጫ ጋር የጡረታ አበል መክፈያ ደብተር ማቅረብ አለበት፡፡

   ለ) የመብት ተጠቃሚ በግል ገቢ በሚያስገኝ ወይም የንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ለባለሁለት እና ለባለሦስት እግር ልዩ ተሽከርካሪ ሲሆን ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ

40,000 ብር (ብር አርባ ሺህ) እና ባለአራት እግር ተሽከርካሪ ሲሆን ደግሞ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 80,000 ብር (ብር ሰማንያ ሺህ) መሆኑን የሚሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ሚረጋገጫ ሚቅረብ አለበት፡፡

7. የመብቱ ተጠቃሚ ከዚህ በፊት በስሙ ምንም ዓይነት የግል ማልገያ ተሽከርካሪ በቀረጥ ነፃ ያላስገባ ሚሆኑን እና በቀረጥ ነፃ የሚስገባዉን ልዩ ተሽከርካሪ እራሱ አካል ጉዳተኛው የሚሽከረከር እንዲሁም ለግል አገልግሎት ብቻ የሚጠቀምበት ለሚሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚዘጋጀው ቅጽ ላይ ሚረጋገጥ አለበት፡፡

8. በተሽከርካሪው አካል ላይ ከሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሚደረገዉን ልዩ ምልክት በፍቃደኝነት የሚቀበል ሚሆኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3 እና 4 ላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ከዋናው ሰነድ በተጨሜሪ ሰነዶቹን ከሰጡት መ/ቤቶቹ ቅጂ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሚድረስ አለበት፡፡

10. የመብቱ ተጠቃሚ ልዩ ተሽከርካሪዉን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሚስገባት የሚችለው በአካል ቀርቦ የሚጠበቅበትን ቅድመ ሁኔታዎች ሚሟላት ሲችል ብቻ ሲሆን ሚፍቸዉንም ተግባር በወኪልና ሚከናወን አይቻልም፡

## ክፍል ሦስት

## <u>መሜሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 7. <u>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

1. የመብቱን ተጠቃሚዎች በልዩ ሁኔታ ለሚስተናገድ እንዲቻል የተለየ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሚስፈፀሚያ ኮድ (Customs Procedure Code) ሚዘጋጀት እና ዲክለራሲዮን ተሞልቶ ደጋፊ ሰነዶቹ ተያይዘው ሲቀርቡ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀም ሚድረግ አለበት፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በቀረጥና ታክስ ነፃ ለሚስተናገድ እና ልዩ ተሽከርካሪዉን ለሚረከብ በአካል እንዲቀርብ ሚድረግ አለበት፡፡

3. የመብቱ ተጠቃሚ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መሜሪያም ሆነ በሌሎች መሜሪያዎች በስሙ የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያላስገባ ስለሚሆኑ በስም፣ በTIN እና በCPC ያረጋግጧል፡፡

4. የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መሜሪያ የተጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች በሚሉ ሚሟላቱ ሲረጋገጥ ልዩ ተሽከርካሪዉን ለሚስገባት የሚያስችለዉን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እንዲችል ለሚመለከተው

ባንክ የቀረጥ ነፃ መብቱ የተፈቀደለት መሆኑን በደብዳቤ ይገልፃል፣ ይህንኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

5. በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በሚያጋግጥ የመብቱ ተጠቃሚ አንድ ልዩ ተሽከርካሪ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲያስገባ ያደርጋል፡፡

6. ከቀረጥ ነፃ የገቡትን ልዩ ተሽከርካሪዎች በተመለከተ አስፈላጊውን ሚረጃ በሚደራጀት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተገቢው ዓላማ እየዋሉ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡

7. የመብቱ ተጠቃሚ ይህን መመሪያ ወይም ሌሎች የጉምሩክ ሕጎችን ጥሶ ሲገኝ ልዩ ተሽከርካሪውን በሕግ ቁጥጥር ሥር በማዋል አሰፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት ልዩ ተሽከርካሪዎች ወደ ሌላ ወገን ለማስተላለፍ የተቀመጡ ማስፈርቶችን መሟላታቸውን በመቆጣጠር እና አስፈላጊውን ሚረጃ በማያዝ ያስፈፅማል፣ ይህንኑ ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

## 8. <u>የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

1. በአካል ጉዳተኞች የሚቀርቡ የሕክምና ማስረጃዎችን በመመርመር፣ በሕግ ዕውቅና ከተሰጣቸው እና ከሚመለከታቸው የአካል ጉዳተኞች ተቋማት ጋር ሚረጃ በማለዋወጥ እና ተገቢውን ምርመራ እና ቁጥጥር በሚደረግ የመብቱ ተጠቃሚ አካል ጉዳተኛ መሆኑን እና ተገቢውን ምርመራ እና ቁጥጥር በሚደረግ የመብቱ ተጠቃሚ አካል ጉዳተኛ መሆኑን እና የጉዳቱን ዓይነት በመጥቀስ የድጋፍ ደብዳቤ ዋና ቅጂ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሚኒስትሩ ይልካል፣ ትክክለኛነቱን ለማምሳከር የዋናውን ሰነድ ቅጂ በፋክስ ሜልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ መሠረት ላስገባው ልዩ ተሽከርካሪ ዓመታዊ ዕድሳት የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ ዋና ቅጂ በፋክስ ሜልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለዓመታዊ ዕድሳት ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮዎች የድጋፍ ደብዳቤዎች የተፃፈላቸውን እንዲሁም በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ ተሽከርካሪ አስገብተው ለዓመታዊ ዕድሳት የድጋፍ ደብዳቤ ያላፃፉትን የመብት ተጠቃሚዎች በማለየት ዝርዝራቸውን ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የዕድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ወስጥ ለሚኒስትሩ እና ለባለሥልጣኑ ይልካል፡፡

4. በዚህ መመሪያ መሠረት የልዩ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ በማስገባት ተጠቃሚ የሚሆኑ አካል ጉዳተኞችን ዝርዝር መረጃ ያደራጃል፡፡

## 9. የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች

1. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ የመብቱ ተጠቃሚ አካል ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ልዩ ተሽከርካሪዎች ማሽከርከር እንደሚችል የሚያሳይ የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፍቃድ የሰጠበትን ቀን፣ ወር እና ዓመት ምህረት እንዲሁም የመንጃ ፈቃዱ የታደሰ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ዋናውን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ይልካል፣ ትክክለኛነቱን ለመመሳከር የዋናውን ሰነድ ቅጂ በፋክስ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል፡፡

2. በቀረጥ ነፃ የተፈቀደውን ልዩ ተሽከርካሪ ለመለየት የሚያስችል በተሽከርካሪው አካል ላይ በሚታይ ቦታ ልዩ ስሌዳ ወይም ሊለወጥ የማይችል ልዩ ምልክት ያደርጋል፡፡

3. የሚመለከተው የትራንስትፖር ቢሮ በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ለዓመታዊ ዕድሳት ሲቀርቡ ከሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ የሚቀርቡትንም የድጋፍ ደብዳቤዎች ዋና ቅጂ በፋክስ መልዕክት እንዲረጋገጡ ያደርጋል፡፡

4. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለዓመታዊ ዕድሳት የቀረቡ የመብት ተጠቃሚዎችን እና የተሽከርካሪዎቻቸውን ዝርዝር የዓመታዊ ዕድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ለሚኒስትሩ እና ለባለሥልጣኑ ይልካል፡፡

## 10. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

1. ለአካል ጉዳተኞች የሐኪሞች ቦርድ መረጃ ለመስጠት የሚችሉ ዕውቅና ያላቸውን ሆስፒታሎች በመለየት ዝርዝራቸውን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስተላልፋል፡፡

2. የሜዲካል ቦርድ መረጃ ለአካል ጉዳተኞች መስጠት ያቆሙ ወይም እንዲያቋርጡ የተደረጉ ሆስፒታሎችን ዝርዝር በወቅቱ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያሳውቃል፡፡

3. የጤና ምርመራ ያደረገው ሆስፒታል የሐኪሞች ቦርድ የሕክምና ማስረጃውን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋናውን ቅጅ ሲልክ ቅጂውን በፋክስ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

## 11. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱ ተረጋግጦ አንድ ልዩ ተሽከርካሪ እንዲያስገባ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ከተፈቀደ በኋላ ተሽከርካሪውን ለመግዛት የሚያስችለውን የውጭ ምንዛሬ እንዲያገኝ ለማስቻል ለሚመለከታቸው ባንኮች ወጥ መመሪያ ያስተላልፋል፡፡

## 12. የፖሊስ አካላት

ከቀረጥ ነፃ የገቡ ልዩ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው ዓላማ ዉጪ ወለው በማኘታቸው እንዲያዙ ከባለሥልጣኑ የትብብር ጥያቄ ሲደርሰው ተሽከርካሪዎችን በማያዝ በአቅራቢያ ላለው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ እና የድርጊቱ ተሳታፊዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በማስወቅ ይተባበራል፡፡

## 13. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት የሚላኩ ሪፖርቶችን እና ሚጃዎች ይቀበላል፣ ይመረምራል፡፡

2. በሚቀርቡ ሪፖርቶች እና ሚጃዎች መሠረት ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጋር በመሆን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

# ክፍል አራት

# ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ልዩ ተሽከርካሪዎች ስለሚተላለፉበት ሁኔታ

## 14. ልዩ ተሽከርካሪዎችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ

1. በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባውን ልዩ ተሽከርካሪ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው ቢያንስ ተሽከርካሪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቆ ለነፃ ዝውውር ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት በኋላ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው፡-

   ሀ) ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለውና የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟላ አካለ ጉዳተኛ ብቻ ነው፡፡

ለ) ሆኖም ልዩ ተሽከርካሪው የሚተላለፈው ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሌላ ሰው ከሆነ ባለው የጉምሩክ ሕግና መመሪያ መሠረት ከተሽከርካሪው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ተደርጎ የሚሰላውን ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በመክፈል ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ሰው የ5 ዓመት የጊዜ ገደቡ ከመድረሱ ወይም ከማጠናቀቁ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት በሚቀርበት የወራሽነት ማረጋገጫ መሠረት ወራሹ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ከመኪናው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ከተደረገ በኋላ በሚከፈለው ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ አስፈላጊ የሆነውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲከፈል ተሽከርካሪው ለሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ቀረጥና ታክሱን መክፈል ካልቻሉ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በማስወረስ ልዩ ተሽከርካሪው ተሸጦ ከሽያጭ ዋጋው ላይ ቀረጥና ታክሱ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲሰጠው/ጣቸው ማድረግ ይቻላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ልዩ ተሽከርካሪን ከመብት ተጠቃሚ ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለው በተጠቃሚው ወይም በሕጋዊ ወራሹ ወይም ወራሾቹ የጽሑፍ ማመልከቻ እና አስፈላጊ ማስረጃዎች ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ

### 15. ክልከላ

1. ማንኛውም የመብት ተጠቃሚ በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች መመሪያዎች በስሙ የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገባ ከሆነ በድጋሚ ልዩ ተሽከርካሪ ማስገባት አይችልም፡፡

2. የሌላ አገር ዜጋ የሆነ ትውልደ ኢትዮጵያዊ አካል ጉዳተኛ በቋሚነት ኢትዮጵያ ለመኖር ወደ አገር ጠቅልሎ መግባቱን፣ ይኖርበት ከነበረው አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የተሰጠ ማስረጃ ሲያቀርብ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ በቋሚነት ቢያንስ አንድ ዓመት የኖረ ስለመሆኑ ከሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር በደብዳቤ ማረጋገጫ ሲያቀርብ እና በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት ሁኔታዎችን ሲያሟላ አንድ ልዩ ተሽከርካሪ በቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

## 16. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ መሠረት ልዩ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገባ የመብት ተጠቃሚ ተሽከርካሪውን ከራሱ ወጪ በሌላ ሰው ሲሽከረከር እና በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ወጪ ለሌላ ጥቅም ቢውል ወይም ለሌላ ወገን ተላልፎ ቢገኝ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና ሰርኩላሮች

በዚህ መመሪያ የተሟለከቱትን ጉዳዮች የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች ወይም የአሠራር ልምዶች ተፈፃሚነት የላቸውም፡

## 18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ _________ ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ______ ቀን 2007 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር